# ትምህርት 47

1. ኢየሱስ የተወለደው በየትኛው ከተማ ነበር?

ሀ- በቤተልሔም ከተማ።

2. ጠቢባኑ የአይሁድ ንጉሥ ያሉትን ኢየሱስን ባገኙት ጊዜ ምን አደረጉ?

ሀ- ሰገዱለት።

ለ- ስጦታዎችንም ሰጡት።

3. ጠቢባኑ ለኢየሱስ ስለሰገዱ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነበር?

ሀ- አልተቆጣም።

4. ጠቢባኑ ለኢየሱስ በመስገዳቸው እግዚአብሔር ያልተቆጣው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

5. መልአኩ ንጉሥ ሄሮድስ ኢየሱስን እንዳይገድለው ማርያምንና ኢየሱስን ዮሴፍ ወደየትኛው አገር ይዞ እንዲሄድ ነገረው?

ሀ- ወደ ግብፅ።

6. ንጉሥ ሄሮድስ ኢየሱስን እንዲገድል ያሳሰበው ማን ነበር?

ሀ- ሰይጣን።

7. ሰይጣን ኢየሱስን ለመግደል የፈለገው ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም ሰይጣን ኢየሱስ ሰዎችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል እንዲያድናቸው ስላልፈለገ ነው።

8. እግዚአብሔር ኢየሱስን የጠበቀው ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ኢየሱስ ሰዎችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል እንዲያድናቸው ስለላከው ነው።

- እግዚአብሔር ኢየሱስን ስለ ጠበቀው ኢየሱስ ከሕፃንነት ጠንካራ ልጅ ወደ መሆን አደገ።

ሉቃስ 2፡40

40- ሕፃኑም እያደገና እየጠነከረ ሄደ፤ በጥበብ ተሞላ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ።

- ኢየሱስ ኃጢአት ሠርቶ ያውቃል?
- አያውቅም።

- ኢየሱስ ሁሉንም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ፈጽሟል ኃጢአትም አልሠራም።

- ኢየሱስ ሁሉንም የእግዚአብሔር ትእዛዝ የፈጸመውና ኃጢአት ያልሠራው እንዴት ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ኃጢአተኛ ሆኖ ስላልተወለደ ነው።

- ኢየሱስ ኃጢአተኛ ሆኖ ያልተወለደው እንዴት ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ የሰው አባት የዘር ፍሬ ስላልነበረው ነው።
- ምክንያቱም ኢየሱስ የሰው እናት የዘር ፍሬ ስላልነበረው ነው።

- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- ኢየሱስ የአዳምና የሔዋን ልጅ ሆኖ ስላልተወለደ ኃጢአተኛ ሆኖ አልተወለደም።

- ኢየሱስ የአዳምና የሔዋን ልጅ ሆኖ ስላልተወለደ ከእግዚአብሔር ተለይቶ አልተወለደም።

- ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በሙላት ታዝዟል።

- ኢየሱስ ስሕተት የሆነን ነገር በፍጹም አላሰበም።
- ኢየሱስ ስሕተት የሆነን ነገርበፍጹም አልተናገረም።
- ኢየሱስ ስሕተት የሆነን ነገር በፍጹም አልሠራም።

- እንደ ኢየሱስ ኃጢአት ያልሠራ ሰው አለ?
- የለም።

- ሌሎች ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኛ ሆነው ተወልደዋል።

- ኢየሱስ ገና ልጅ ስለ ነበረበት ጊዜ የሚናገረውን ታሪክ እንመልከት።

ሉቃስ 2፡41

41- የኢየሱስ ወላጆቹም በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር።

- በየዓመቱ የኢየሱስ ወላጆች ዮሴፍና ማርያም የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር።

- ኢየሱስ የ12 ዓመት ልጅ በነበረበት ጊዜ ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስን ወደ ኢየሩሳሌም ይዘውት ሄዱ።

## ሉቃስ 2፡42

42- የኢየሱስ ዐሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ፣ እንደ ተለመደው ወደ በዓሉ ወጡ።

- የፋሲካ በዓል ካበቃ በኋላ ዮሴፍና ማርያም ወደ ቤታቸው ወደ ናዝሬት መመለስ ጀመሩ።

- ነገር ግን ዮሴፍና ማርያም ብዙ ከተጓዙ በኋላ ኢየሱስን ከአጠገባቸው ሊያገኙት አልቻሉም።

## ሉቃስ 2፡43-44

43- በዓሉን ከፈጸሙ በኋላ፣ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀረ፤ ወላጆቹ ግን መቅረቱን አላወቁም ነበር።

44- አብሮአቸው ያለ መስሎአቸው፣ የአንድ ቀን መንገድ ተጓዙ፤ በኋላ ግን ከዘመዶቻቸውና ከወዳጆቻቸው ዘንድ ይፈልጉት ጀመር።

- ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስን ሊያገኙት ያልቻሉት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ብዙ አይሁዶች በፋሲካው በዓል ላይ ስለ ተገኙ በመንገድ ላይ እጅግ ብዙ ሕዝብ ስለ ነበር ነው።

- ምክንያቱም በመንገድ ላይ ብዙ ዘራፍዎች ስለ ነበሩ ሰዎች የሚጓዙት በኅብረት ስለ ነበር ነው።

- ምክንያቱም በዚያ እጅግ ብዙ ሰዎች ስለነበሩ ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስን ማየት ስላልቻሉ ነው።

- ምክንያቱም እጅግ ብዙ ሰዎች በዚያ ስለ ነበሩ ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስ ከጓደኞቹ ጋር አብሮ እንደ ሄደ ስላሰቡ ነው።

- ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር እንዳልነበረ ባወቁ ጊዜ ምን አደረጉ?

ሉቃስ 2፥45

45- ባጡትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።

- ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስን ለመፈለግ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።
- ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስን ያገኙት የት ነበር?

ሉቃስ 2፥46-47

46- ከሦስት ቀንም በኋላ፣ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲያዳምጣቸውና ጥያቄ ሲያቀርብላቸው በቤተ መቅደስ ውስጥ አገኙት፤
47- የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና በመልሱ ይደነቁ ነበር።

- ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስን በኢየሩሳሌም በቤተ መቅደስ ውስጥ አገኙት።

- ዮሴፍና ማርያም በቤተ መቅደስ ውስጥ ሲያገኙት ኢየሱስ ምን ያደርግ ነበር?

- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል መምህራንን እያዳመጠና ጥያቄ እየጠየቃቸው ነበር።

- ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል ለመምህራን እያስተማራቸው ነበር።

- ኢየሱስ ገና የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሆኖ የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት አወቀ?

- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበሩት መምህራን ኢየሱስ ስላለው የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ይደነቁ ነበር።

- እነርሱ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን አላወቁም።

- በቤተ መቅደስ ውስጥ ባገኙት ጊዜ ማርያም ኢየሱስን ምን አለችው?

ሉቃስ 2፡48

48- ወላጆቹም ባዩት ጊዜ ተገረሙ፤ እናቱም፣ «ልጄ ሆይ፤ ለምን እንዲህ አደረግኸን? አባትህና እኔኮ ተጨንቀን ስንፈልግህ ነበር» አለችው።

- ኢየሱስ ለዮሴፍና ለማርያም ምን መለሰላቸው?

ሉቃስ 2፡49

49- እርሱም «ለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት መገኘት እንደሚገባኝ አላወቃችሁምን?» አላቸው።

- ማርያም በጠየቀችው ጊዜ ኢየሱስ ምን አለ?

- ኢየሱስ «በአባቴ ቤት መገኘት እንደሚገባኝ አላወቃችሁምን?» አላቸው።

- ኢየሱስ እንዲህ ሲል ምን ማለቱ ነበር?

- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ እንዲሠራ የፈለገውን ሥራ እየሠራ እንደ ነበር ተናገረ።

- ኢየሱስ ዕድሜው ዐሥራ ሁለት ዓመት ብቻ ቢሆንም እግዚአብሔር አብን አውቋል።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ እንዲያደርግ የነገረውን ሁሉ ፈጽሟል።

- ኢየሱስ ያሰበው ሁሉ ፍጹም ነበር።
- ኢየሱስ የተናገረው ሁሉ ፍጹም ነበር።
- ኢየሱስ ያደረገው ሁሉ ፍጹም ነበር።

- ኢየሱስ የተናገረውን ዮሴፍና ማርያም ተረድተዋል?

ሉቃስ 2፥50

50- እነርሱ ግን የተናገራቸው ነገር አልገባቸውም።

- ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስ የተናገራቸው ነገር አልገባቸውም።

- ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር አብ እየተናገረ እንደ ነበር አላስተዋሉም ነበር።

- ንግግራቸውን እንደ ጨረሱ ዮሴፍ ማርያምና ኢየሱስ ወደ ቤታቸው ወደ ናዝሬት ተመለሱ።

## ሉቃስ 2፥51-52

51- ከዚያም አብሮአቸው ወደ ናዝሬት ወረደ፤ ይታዘዝላቸውም ነበር። እናቱም ይህን ሁሉ ነገር በልቧ ትጠብቀው ነበር።

52- ኢየሱስም በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አደገ።

- ኢየሱስ በማደግ ላይ በነበረበት ወቅት ለዮሴፍና ለማርያም በትክክል ይታዘዝ ነበር?

- አዎን።

- ምንም እንኳ ኢየሱስ እንደ ሌሎች ልጆች ቢሆንም ከሌሎች ልጆች የሚለየው በምን ነበር?

- ኢየሱስ እግዚአብሔር በመሆኑ።

- ኢየሱስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በመሆኑ።

- ኢየሱስ ጠቢብ ሰው ሆኖ አደገ።

- እግዚአብሔር ከብዙ ዘመናት በፊት በነቢያት አማካይነት በተናገረው መሰረት ኢየሱስ ታላቅ ጥበብ ነበረው።

- እግዚአብሔር ከረጅም ዘመናት በፊት በነቢያት አማካይነት እንደተናገረ፥ ኢየሱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር።

- እግዚአብሔር በፍጹም የተስፋ ቃሉን አያጥፍም።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ የተስፋ ቃሉን ይጠብቃል።